# ሥልጣንን ከድምፅ ኮሮጆ ሳይሆን ከሁከት ማግኘት የሚመኝ ፓርቲ

## ክፍል ሁለት

ኢብሳ ነመራ

07-23-14

በዚሁ ርዕስ ባቀረብኩት ክፍል አንድ ፅሁፍ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሰሞኑን በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉ ግለሰቦችን ጉዳይ መነሻ በማድረግ የወጣውን መግለጫ የተወሰነ ክፍል አቅርቤ ነበር። የተቀረው መግለጫ ላይ ያለኝን አስተያየት ደግሞ በዚህ ፅሁፍ አቀርበዋለሁ።

አንድነት ባወጣው መግለጫ "መንግስት እየወሰደ ነው" ያለውን የፈጠራ እርምጃ አስመልክቶ "የዚህ አይነቱ እርምጃ ፓርቲዎች መሰብሰብ ብሎም መዋሃድ ሲጀምሩ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ከዚህ ቀደም ያስተዋልነው ድርጊት ነው" ይላል።

የፓርቲዎች መመስረትና ውህደት መፍጠር በገዢው ፓርቲ ችሮታ የሚሰጥና የሚነፈግ ሳይሆን ሕገመንግስታዊ መብት ነው። ከዚህ ቀደም አንዳንዴ ውጭ ሃገር ባሉ የገንዘብ ደጋፊዎች ጭና፣ ሌላ ግዜ ደግሞ ሃገር ውስጥ ባሉ ልሂቃን ግፊት ተቃዋሚዎች ውህደት መስርተዋል። አንድነት ከዚህ አይነት ውህደት መስራች ፓርቲዎች መሃከል ቀዳሚው ነው። አንዴም ለምን ውህደት መሰረተታችሁ በሚል የተቃወማቸው አልነበረም።

ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ውህደቶች ከፓርቲዎቹ ውስጣዊ ግፊት የተፈጠሩ ስላልነበሩ፣ በአቋምና በአላማ ላይ የተመሰረቱ ውህደቶች/ጥምረቶች አልነበሩም። በመሆኑም እንደ አሸዋ ካብ መፈራረስ ዋና መገለጫቸው ነበር።

አንድነት ከዚህ ቀደም ከመድረክ ጋር ተጣምሮ ነበር። ጥምረት ውስጥ የገባው ግን መድረክን ከመሰረቱት በብሄር ላይ ተመስርተው የተደራጁ ፓርቲዎች ጋር ተመሳሳይ አቋምና አመለካከት ስልነበረው አይደለም። በዚህ ሁኔታ ያለአላማ መመሳሰል አንድነት

የተቀላቀለው ጥምረት በኋላ ወደ ውህደት መሸጋገሩንም ሰመተን ነበር። አንድነት በአንድ በኩል ከማይመሳሰሉት የመደረክ ፓርቲዎች ጋር መዋሃዱን እየተናገረ፣ በጎን ደግሞ ራሱን ችሉ ብርሃን ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ከተባለ ፓርቲ ጋር ተዋህዶ ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማንም "ለምን ተዋሃዳችሁ?" ብሎ የጠየቀም የከለከለም አለነበረም። ሕገመንግስታዊ መብት ስለሆነ። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የውህደት ጥያቄያቸውን ተቀብሎ በሕጉ መሰረት ለውህደታቸው ጥያቄ ሕጋዊ እውቅና ሰጥቷቸዋል። እነዚህ እውነታዎች መንግስት እና/ወይም ገዢው ፓርቲ የፓርቲዎችን መዋሃድ እነደችግር ተመልክቶ እንደማያውቅ፣ ይህንን የሚያሰናክል እርምጃ የመውሰድ ፍላጎት እንደሌለው ያረጋግጣሉ።

ከዚህ ቀደመ በፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሰረቱ ከተባሉ ጥምረቶችና ውህደቶቸ መሃከል አለሁ ቸለሁ በሚሉት ፓረቲዎች የተመሰረቱት፣ ከአላማ መመሳሰልና ከውስጣዊ ግፊት ይልቅ በውጫዊ ጫና የተመሰረቱ ስለነበሩ ገና የውህደት ሥምምነታቸው ፊርማ ቀለሙ ሳይደርቅ ወደጭቅጭቅና መለያየት ተሸጋገረዋል። ውህደትን በተመለከተ በአንድነትም ሆነ በሌሎች ፓርቲዎች ዙሪያ ያለው ችግር ውስጣዊ እንጂ ከገዢው ፓርቲ የመነጨ አልነበረም።

አንድነት ሰሞኑን ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጋር ውህደት ሊመሰርቱ መሆኑን ነግረውናል። ገና ውህደቱ ሳይመሰረት "ውህደታችን ገዢውን ፓርቲ አስፈርቶታል" የሚለው ወሬ ቀድሟል። አንድም አካል ግን "ለምን ውህደት መሰረታችሁ?" አላላቸውም። ውህደታቸው በኋላ ወደመወቃቀስ፣ በድንጋይና በዱላ ወደመከታከት እንዳይቀየር ከመስጋት ያለፈ ሁሉም "ያብጅላችሁ" ነው ያላቸው፤ ገዢውን ፓረቲ ጭምር።

የአንድነት አመራሮች አንድን የፓለቲካ ፓርቲ የህዝብ ይሁንታ ያለውና ጠንካራ ተፎካካሪ የሚያደርገው የተለያዩ ፓርቲዎች ውህድ መሆኑ ብቻ አለመሆኑን ማወቅ አለባቸው። ለስልጣን የሚያበቃ የህዝብ ይሁንታ ማግኘት የሚያስችለው በመላው አገሪቱ የሚገኙ የተለያየ ቀንቋ፣ ባህልና ወግ ያላቸውን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት

ማስከበር የሚችል፣ ሰላምን ማረጋገጥ፣ በልማት የተሻለ ሕይወት መኖር የሚያስችል ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ተጨባጭ አቋምና ፖሊሲ ብቻ ነው።

አንድነትን ከዚህ አኳያ ሥናየው የፖለቲካ ፖሊሲው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ላለው የብሄራዊ መብትና ነፃነት እውቅና የማይሰጥ ነው። በዚህ ምክንያት ከብሄራዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ ለሚመነጩ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር፣ በቋንቋ የመስራት፣ የመማር፣ ታሪክንና ባህልን የማሳደግና የማስተዋወቅ . . . መብትና ነፃነቶችን አይቀበልም።

የኢኮኖሚ ፖሊሲውም ቢሆን 85 በመቶ የሚሆነው የአገሪቱ ሕዝብ የተሰማራበትና እስካሁን ባለው ሁኔታ የአገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውን ግብርና ማሳደግ፣ የአርሶአደሩን ሕይወት ወደተሻለ ደረጃ መሻገርና ዘርፉ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች መፈጠርና እድገት የካፒታል ክምችት መፍጠር በሚያስችልበት ሁኔታ መምራት የሚያስችል ፖሊሲ የለውም። አንድነት አሁን ባለው የአገሪቱ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ "በአንድ ግዜ ኢንደስትሪ መር የኢኮኖሚ እፈጥራለሁ" ባይ ነው።

የኢንደስትሪ ኢኮኖሚ በአንድ ሃገር በተጨባጭ ካለ ሃብት ላይ የካፒታል ክምችት በመፍጠር የሚደረስበት የእድገት ደረጃ እንጂ እንደመና ድንገት ከሰማይ የሚወርድ አይደለም። ኢንደስትሪ መር ኢኮኖሚ በተጨባጭ በእጅ ካለ ሃብት የካፒታል ክምችት በመፍጠር፣ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በማፍራት የሚደርስበት እንጂ በአዋጅ የሚመጣ አይደለም።

በመሆኑም አንድነት አሁን በያዘው አቋሙና ፖሊሲው የጥቂት የተምታታባቸው ከተሜዎችን ካልሆኑ የአብላጫውን የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ ማግኘት የሚችል ፓርቲ አይደለም።

ታዲያ አንድነት በዚህ ፖሊሲው ከመሰሉ ጋር ቢዋሃድ በሚያገኘው የህዝብ ይሁንታ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ በተለያየ ቋት ያለ ቆሻሻ በአንድ ቋት ውስጥ ቢገለበጥ ትልቅ ቆሻሻ እንጂ ጭብጥ እህል አይወጣውምና። ሥለዚህ ገዢው ፓርቲም ሆነ ሌሎች ከአንድነት የተለየ ፖሊሲ ያላቸው ፓርቲዎች አንድነት ከመሰሎቹ ጋር የሚያደርገው

ውህደት ተፎካካሪ ይፈጥርብኛል በሚል የሚያሰጨንቃቸው አይደለም፡፡ አንድነት "ውህደት ለመሰርት ሥል ገዢው ፓርቲ ተጨነቀ" በሚል በመግለጫው ላይ ያወራው ራሱን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ የማይመከት መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት ሥለራሱ ያለው ግንዛቤ የተዛባና ግብዝ መሆኑን ያመለክታል።

አንድነት በመግለጫው "ምርጫ ሲደርስ የሚጨነቀው ገዢው ፓርቲ፣ አባሎቻችንን መደብደብና ማሳደድ አልበቃ ብሎት በምርጫው ዋዜማ በተለመደውና አሰልቺ ፍረጃው ተደግፎ አመራሮችን ማሰር ጀምሯል።" ይላል። በቅድሚያ አንድነት አመራሮቼ የሚላቸው ሰዎች የታሰሩት በፓርቲው አባልነታቸው ሳይሆን በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ለጥርጣሬ የሚያበቃ ማስረጃ በመኖሩ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ከዚህ በተረፈ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት በተለይ አንድነት በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን መብት፣ ነፃነትና ጥቅም የሚያስጠብቅ ፖሊሲ ስለሌለው ኢህአዴግን የመፎካከር ብቃት ያለው ፓርቲ አይደለም። በአጠቃላይ አንድነት በምርጫ የህዝብን ይሁንታ አግኝቶ ወደስልጣን ለመውጣት የሚሰራ የምርጫ ፓርቲ አይደለም። አንድነት ምርጫ ላይ ተወዳድሮ ከድምፅ ኮሮጆ ፅልጣን ለማግኘት የሚሰራ ፓርቲ ሳይሆን፣ በየወቅቱ የሚያጋጥሙ የህዝብን ስሜት ሊኮረክሩ ይችላሉ ያላቸውን ጉዳዮች የፖለቲካ አጀንዳ በማድረግ ህዝብን በማደናገር በህዝባዊ ንቅናቄ/ሁከት ወደስልጣን እወጣለሁ ብሎ የሚያስብ ፓርቲ ነው። በመሆኑም ገዢው ፓርቲ የምርጫ ፓርቲ ያልሆነው አንድነት በምርጫ ይገዳደረኛል ብሎ ምርጫ ሲደርስ እንዲጨነቅ የሚያደርገው አንዳችም ምድራዊ ምክንያት የለም።

ባለፉት አስርት አመታት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ኢህአዴግ ምርጫ ሲቃረብ ጥቃቅን ጫሂ አጀንዳዎችን እያቃረመ ለህዝብ አሳቢ መስሎ ለመታየት የሚዋከብ የቁጥቁጥ ፓርቲ አይደለም። ኢህአዴግ የሩቅ ግብ አልሞ ወደዚህ የሩቅ ግቡ ሊያደርሰው የሚችለውን አቅጣጫና አካሄደ አንጥሮ አስቀምጦ፣ የሚጓዝ በጥቃቅን ጉዳዮች የማይናወጥ ፓርቲ ነው።

ደርግን የሚያህል በአፍሪካ በወታደራዊ አቅም የሚፎካከረው የለም የሚባለውን ኃይል መደምሰስ የቻለው በዚህ ሩቅ ዓልሞ የእርምጃዎቹን አቅጣጫ አውቆ የመንቀሳቀስ አካሄዱ

ነው። በደርግ ውድቀት ማግስት “አገሪቱ ትፈርሳለች” ተብሎ ሲሰጋ፣ ይህን ክፉ ቅዠት ከንቱ አድርጎ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በመከባበርና በእኩልነት የሚኖሩባትን አዲሲቱን ሰላማዊ ኢትዮጵያ መገንባት የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ባለፉት አስር ተከታታይ አመታት በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ የቻለው፣ የሩቅ ግብ አልሞ ወደዚህ የሩቅ ግቡ ሊያደርሰው የሚችለውን አቅጣጫና አካሄድ አንጥሮ አስቀምጦ የሚጓዝ ፓርቲ በመሆኑ ነው።

ፈራርሳ በነበረችው ሶማሊያ የዓለም አቀፍ አሸባሪው አልቃይዳ የአፍሪካ ክንፍ የሆነው አልሸባብ ኢትዮጵያን ኢላማው አድርጎ መንቀሳቀስ ሲጀምር ይህን እንቅስቃሴ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ ከሶማሊያ የሽግግር መንግስት ጋር በመተባበር ቦታው ድረስ ሄዶ ማክሸፍ የቻለው አርቆ አሳቢ ፓርቲ በመሆኑ ነው። ከህዝብ ፍላጎት ውጭ አንድን ብሄር በመገንጠል ነፃ መንግስት እንመሰርታለን የሚሉና ግንቦት 7ን የመሰሉ ዓላማቸው ምን እንደሆነ የማይታወቅ በጭፍን ጥላቻ የሚነዱ ዘረኛ ቡድኖች ከሻእቢያ ጋር በማበር በሽብር አገሪቱን ለመናጥ የሚያደርጉትን መሹልክለክ ማመከን የቻለውም ለዚህ ነው። አክራሪነት መሰረቱን ጥሎ እስላማዊ መንግስት የመመስረት ህልም ይዞ ለመንቀሳቀስ በሚፍጨረጨርበት ሁኔታ በእነዚህ ኃይሎች ሊደርስ የሚችል የሽብር ጥቃትን በአስገራሚ ድንቅ ብቃት መክቶ ኢትዮጵያን በሰላም ምሳሌነት የምትጠቀስ አገር ማድረግ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ከሶስት አመት በፊት የተጀመረውን ታላቅ አገራዊ መግባባት የተፈጠረበትን የህዳሴ ግድብ ማስገንባት የጀመረውና ግንባታው እንደሚጠናቀቅ አስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ኢህአዴግ እነዚህንና መሰል ሩቅ አሳቢነትን የሚጠይቅ ስትራቴጂያዊ አካሄድ ዋና መለያው ነው። ለምርጫ ሲቀርብም ይህንኑ ስትራቴጂውን ነው ይዞ የሚቀርበው። በቀጣይ ምርጫ ላይ ይዞ የሚቀርበው እስካሁን የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት፣ ሰላም ፣

ዴሞክራሲ አስቀጥላለሁ ከሚል ውጭ እንደማይሆን እርግጠኛ ነው። ኢህአዴግ አንድነት በመግለጫው ሊነግረን እንደሞከረው ምርጫ ሲደርስ አጀንዳ እየቃረመ የሚቅበዘበዝ የቁጥ ቁጥ ፓርቲ አይደለም።

ይህ የቁጥ ቁጥ አካሄድ የአንድነት ባህሪ ነው። ምርጫ ሲደርስ መዋከብ፣ ህዝብ በገገርው ፓርቲ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት ማድረግ የሚያስችል አጀንዳ በማነፍነፍ በየሳምንቱ የተለያየ፣ አንዳንዴም እርስ በርሱ የሚጣረስ መግለጫ በማውጣት፣ የተቃውሞ ሰልፍ በመጥራት የኢህአዴግ ሳይሆን የአንድነት ባህሪ ነው። አንድነት የስትራቴጂ ፓርቲ ሳይሆን ነገ ምን እንደሚሰራ የማያውቅ ሁኔታዎች የሚነዱት የተዋከበ የቁጥቁጥ ፓርቲ ነው።

የአክራሪነት ትኩሳት ሞቅ ሲል አንድነት ከዚህ ላይ ቆንጥሮ ለህዝብ ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ጉዳዩን ያራግባል። የኦሮሚያንና የሶማሌ ክልሎችን እንገነጠላለን ብለው ሻዕቢያ ጉያ የተወሸቁ ቡድኖች ያሰማሯቸው አሸባሪዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ ለብሄራዊ መብትና ነፃነት እውቅና የማይሰጠው አንድነት ፓርቲ ደርሶ የኦሮሞ፣ የሶማሌ ተቆርቋሪ ሆኖ አንድ ሳምንት "ይፈቱ ምንትስ ቅብርጥስ" የሚል ወሬ ያናፍሳል። ይህ የአንድነት በየጊዜው የሚይዛቸው የተዘበራረቁ አቋሞች ፓርቲው ሥትራቴጂ ላይ የተመሰረተ ቁመና የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል።

እናም ሰሞኑን በሽብር ወንጀል ተጠርጣሪዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ "ኢህአዴግ ምርጫ ደረሰ ብሎ ተርበትብቶ የወሰደው ነው" የሚለው የአንድነት ወሬ መሰረተ ቢስና የፓርቲውን ምንነት የሚያጋልጥ ነው። በስነምግባር የማይመራው አንድነትን እንደ ሕጋዊ ሽፋን በመጠቀም ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን በሽብርተኝነት ተጠርጥረው የታሰሩ አንድ ሁለት ሰዎችን ጉዳይ፣ "ምርጫውን ለመጠቅለል የተወሰደ" በሚል ባዶ ወሬ ያስወራው ህዝብን ማደናገር እንደሚያስችል መልካም አጋጣሚ በማሰብ ነው።

የአንድነት መግለጫ በመጨረሻም "የአንድነት ከፍተኛ አመራሮች አቶ ሃብታሙ አያሌው አቶ ዳንኤል ሺበሺና ሌሎችም ፖለቲከኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ" ሲል አሳስቧል።

በቅድሚያ አንድም በያዘው አመለካከት ብቻ በቁጥጥር ስር የዋለ “ፖለቲከኛ” የለም። አንድነት አባላቴ ናቸው የሚላቸው በቁጥጥር ስር የዋሉ ግለሰቦች በወንጀል የተጠረጠሩ ናቸው። አንድነት ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተጠረጠሩበት ወንጀል ሳይታወቅ፣ የከሳሽ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ መከላከያ ማስረጃ ሳይሰማ “ሰዎቹ ንፁሃን ናቸው” ማለቱ ስለየህግ የበላይነት ምንም ግንዛቤ እንደሌለው አለያም የህግ የበላይነትን እንደማያከብር ያመለክታል።

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት እውነታዎች፣ አንድነት የምርጫ ፓርቲ አለመሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። በመሆኑም አንድነት የመንግስትን ሥልጣን ከምርጫ ኮሮጆ ሳይሆን ከጎዳና ነውጥና ከሽብር ይገኛል ብሎ ተስፋ ያደረገ ፓርቲነቱ ጎልቶ ይታያል። ይህ አካሄዱ የትም ስለማያደርሰው ራሱን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ቀርያ በህዝብ ይሁንታ ወደስልጣን ለመውጣት ቢንቀሳቀስ ይበልጥ ወደፊት ያራምደዋል። ወደሥልጣን ለመውጣት የሚያስችለው አጭሩ መንገድም ይህ ብቻ ነው።